# የ DENVER የመረጃዎች ጽሁፍ (GUIDE) ለአዳዲስ አሜሪካውያን

DENVER PUBLIC LIBRARY

PLAZA & SERVICES TO IMMIGRANTS AND REFUGEES

# እንኳን ደህና መጡ።

Denver Public Library የእርስዎን አዲስ ስደተኛ፣ ሀገር ጥሎ የሸሸ ሰው፣ ወይም ጥገኝነት የተፈቀደለት ሰው መሆን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ Colorado ላይ ኑሮ ለመመስረት የሚረዳዎት ታማኝ የሆኑ የመረጃ ምንጮች (resources) ሰብስቦ እዚሁ መመሪያ (guide) ላይ አቅርቦሎታል። ይህንን የመመሪያ መጽሀፍ (guidebook) ሙሉ ይዘቱን ወይንም ያስፈልጉኛል የሚሉዋቸው ክፍሎችን መርጠው እንደፍላጎትዎ ሊያነቡት ይችላሉ:


1. ኮሎራዶ ክፍለሀገር ........ 2
2. የመነሻ መረጃ ........ 3
3. የዴንቨር የህዝብ ቤተ ምጽሃፍትቤት ቅርንጫፎች የሚገኙባቸው ቦታዎች ........ 4
4. የቆንስላ ጽህፈትቤቶች ........ 6
5. አጭር ማጣቀሻዎች እና ሪፈራሎች ........ 12
6. የጉዳይ አስተዳዳር/የብዙ አገልግሎት ኤጀንሲዎች ........ 14
7. የአዋቂዎች ትምህርት ........ 17
8. የቤተሰብ እና ህጻናት አገልግሎቶች ........ 19
9. ስራ (Employment) ........ 21
10. ጤና........ 23
11. መኖሪያ ቤት ........ 26
12. አለማአቀፍ የገበያ ማእከሎች ........ 28
13. የህግ ድጋፍ እና ስደት ........ 29
14. የግብር ጉዳዮች ........ 33
15. የትርጉም እና የኢንተርፕሪቴሽን ስራዎች ........ 34
16. የኢንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች ........ 35
17. የአጠቃላይ ትምህርት እድገት (GED) ፈተና መስጫ ማእከሎች እና የትምህርት አይነቶች ........ 36


እርስዎ ወደ አዲስ ሂወት የሚያደርጉት ሽግግር ለማገዝ ሲባል የዴንቨር የህዝብ ቤተምጽሃፍት ለአዳዲስ ስደተኞች የሚሰጣቸው አገልግሎቶች አሉት! በአጎራባችዎ ባለው ቤተመጽሀፍት የምንገኝ ሲሆን የእርስዎን ፍላጎቶች መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች እንሰጣለን። የስደት ሂደቱ መከታተል ከባድ ስራ ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም እርስዎ በሚያደርጉት ልዩ ጉዞ ሁሉ አጋርዎ እንደምንሆን ተስፋ እናደርጋለን።

## እንኳን ወደ ዴንቨር በደህና መጡ!

# ኮሎራዶ ክፍለሀገር



ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች ስንል በህግ የዩ.ኤስ. ዜግነት የተሰጣቸው ሰዎችን ጨምሮ ሁሉንም የዩ.ኤስ. ዜግነት አሜሪካ ውስጥ በመወለዳቸው ሳይሆን በሌላ ምክንያት የተሰጣቸው ሰዎች ያጠቃልላል፡፡

ጠቅላላ የ Colorado ህዝብ ብዛት: 5,456,574
Colorado ውስጥ የሚኖሩ ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች የህዝብ ብዛት: 538,244
ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች ብዛት ከጠቅላላ ህዝቡ በመቶኛ ሲቀመጥ: 10%

ጠቅላላ የ Denver ህዝብ ብዛት: 633,777
Denver ውስጥ የሚኖሩ ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች የህዝብ ብዛት: 101,705
ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች ብዛት ከጠቅላላ ህዝቡ በመቶኛ ሲቀመጥ: 16%

Rev 11/16

# የመነሻ መረጃ




## ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች የእድሜ ክልል

- ከአምስት አመት በታች
- 5-17 አመት
- 18-24 አመት
- 25-44 አመት
- 45-54 አመት
- 55+ አመት

የኮሎራዶ አማካኝ እድሜ የውጭ ሀገረ ተወላጅ ግለሰቦች: 40.7 አመት

የዴንቨር አማካኝ እድሜ የውጭ ሀገረ ተወላጅ ግለሰቦች: 38.1 አመት

## ውጭ ሀገር የተወለዱ ሰዎች ዲሞግራፊክስ

- ላቲን አሜሪካዊ
- ኤዥያዊ/ፓሲፊክ አይላንደር
- አውሮፓዊ
- አፍሪካዊ
- ሰሜን አሜሪካዊ



# የዴንቨር የህዝብ ቤተ ምጽሃፍትቤት ቅርንጫፎች የሚገኙበት

እንደ የባህል ተቋምቱ፣ የቤተመጽሀፍቱ ሀላፊነት ነጻ መረጃ፣ ዝግጅት፣ እና የመረጃ ይዘቶች (materials) መስጠት፣ እንዲሁም ተጠቃሚዎች የተናጠል ፍላጎቶቻቸው ሊያሟሉላቸው ከሚችሉ አካባቢያዊ ድርጅቶች ጋር እንዲገናኙ እገዛ መስጠት ነው። የዴንቨር የህዝብ ቤተምጽሃፍት ፕላዛ ዝግጅት በተለይ ለስደተኞች፣ በሽሽት ሀገራቸው ጥለው የመጡ ሰዎች፣ እንዲሁም ጥገኝነት ለተፈቀደላቸው ሰዎች ፍላጎቶች ምላሽ የመስጠት ሀላፊነት አለው።

ፕላዛዎች (Plazas) ከሁሉም የአለማችን አቅጣጫዎች የመጡ ስደተኞች ከሰዎች፣ ከመረጃ፣ እና ከመረጃ ምንጮች ጋር እንዲገናኙበት ተብሎ የተዘጋጀ ልዩ ቦታ ሲሆን ዋናው ግቡ ደግሞ በ Denver ውስጥ ስኬታማ የሆነ አለምአቀፋዊ ማህበረሰብ መገንባት ነው። ከሁልም የእድሜ ክልል እና ታሪካዊ ዳራ የሆኑ አዳዲስ መጤዎች በሁለተኛ ቋንቋ የመግባባት ክህሎት በሚያዳብረሩበት፣ ለዜግነት በሚዘጋጁበት፣ አዳዲስ የስራ ኔትወርኮች በሚፈጥሩበት፣ እና የስደተኞች ተመኩሮ በተመለከተ ሀሳቦች በሚለዋወጡበት ጊዜ ይህ ፕሮግራም ነጻ እድሎችና ስፔሻላይዝድ የሆነ እገዛ ያቀርብላቸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ ከሚከተሉት ስደተኛ-ተኮር ዝግጅት የሚሰጡ ስፍራዎች መካከል አንዱን ይጎብኙ፣ ወይም ከአገልግሎት ለአዳዲስ ስደተኞች ሀላፊ (Services to New Immigrants administrator) ከሆነው ዊል ቻን ጋር በኢሜይል: wchan@denverlibrary.org, ወይም በስልክ: 720-865-0156 ይገናኙ።

**Athmar Park Branch Library**
*1055 S. Tejon St.*
*Denver, CO 80223*
*(720) 865-0230*

**Bear Valley Branch Library**
*5171 W. Dartmouth Ave.*
*Denver, CO 80236*
*(720) 865-0975*

**Green Valley Ranch Branch Library**
*4856 N. Andes Ct.*
*Denver, CO 80204*
*(720) 865-0310*

**Hadley Branch Library**
*1890 S. Grove St.*
*Denver, CO 80219*
*(720) 865-0170*

**Hampden Branch Library**
*9755 E. Girard Ave.*
*Denver, CO 80231*
*(720) 865-0185*

**Montbello Branch Library**
*12955 Albrook Dr.*
*Denver, CO 80239*
*(720) 865-0200*

**Rodolfo “Corky” Gonzales Library**
*1498 N. Irving St.*
*Denver, CO 80249*
*(720) 865-2370*

**Ross-Barnum Branch Library**
*3570 W. 1st Ave.*
*Denver, CO 80219*
*(720) 865-0145*

**Schlessman Family Branch Library**
*100 Poplar St.*
*Denver, CO 80220*
*(720) 865-0000*

**Valdez-Perry Branch Library**
*4690 Vine St.*
*Denver, CO 80216*
*(720) 865-0300*

# የዴንቨር የህዝብ ቤተ ምጽሃፍትቤት ቅርንጫፎች የሚገኙባቸው ቦታዎች




Rev 11/16 06.13.5M

የተለያዩ አገልግሎቶችን ለአዲስ መጪ ተፈናቃዮች፤ ስደተኞች እና አሳይሊዎች የሚሰጡ ቤተመፅሃፍቶች

# የቆንስላ ጽህፈትቤቶች

* የሙያ አመልካች ኮንሱል

## አውስትራልያ

የክብር ቆንስል *Mark O'Regan*
*8480 E. Orchard Rd., Ste. 1100, Greenwood Village, CO 80111*
*TEL: 303-321-2234, FAX: 303-773-1664, MOBILE: 720-351-8865*
*E-MAIL: koalare1@mindspring.com*

## አውስትሪያ

የክብር ቆንስል *Hikmet Ersek,* ረዳት የክብር ቆንስል *Dr. Nayantara Ersek*
*100 Filmore St., 5ኛ ወለል, Denver, CO 80206*
*TEL: 303-385-8540*
*E-MAIL: info@austrianconsulatedenver.org*

## ባሐማስ

የክብር ቆንስል *Gregory Daniel Treco*
*6430 S. Langdale Way, Aurora, CO 80016*
*TEL: 303-699-1107, MOBILE: 303-522-8470*
*E-MAIL: hcbhs.co@icloud.com*

## ቤልጂም

የክብር ቆንስል *Frank J. Schuchat*
*1888 Sherman St., Ste. 200, Denver, CO 80203*
*TEL: 720-305-9897*
*E-MAIL: Frank@schuchatlaw.com*

## *ካናዳ




ቆንስል ጄነራል *Stephanie Lessard*
የካናዳ ቆንስላ ጄነራል
*1625 Broadway, Ste. 2600*
*Denver, CO 80202*
*www.denver.gc.ca*
*TEL: 303-626-0650*
*E-MAIL: stephanie.lessard@international.gc.ca*

ቆንስል እና ከፍተኛ የንግድ ኮሚሽነር
*Jerome Pischella*
*TEL: 303-626-0667*
*FAX: 303-572-1159*
*E-MAIL: jerome.pischella@international.gc.ca*

ቆንስል እና የንግድ ኮሚሽነር
*Pamela Rose*
*TEL: 303-626-0678*
*E-MAIL:pamela.rose@international.gc.ca*

## ኮስታ ሪካ
የክብር ቆንስል *Tito Chaverri*
*3356 South Xenia St., Denver, CO 80231*
*TEL: 303-696-1182*
*E-MAIL: cronsul@msn.com*

## ቼክ ሪፐብሊክ
የክብር ቆንስል *Robert D. Erben*
*1600 38th St., Ste. 101, Boulder, CO 80301*
*TEL: 303-444-0490*
*E-MAIL: robert@erbenlaw.com*

## ዴንማርክ
የክብር ቆንስል *Nanna Nielsen Smith*
*5353 W. Dartmouth Ave., Ste. 508, Denver, CO 80227*
*TEL: 303-980-9100*
*E-MAIL: hnielsen980@yahoo.com*

## ፊንላንድ
የክብር ቆንስል *Juha V. Mäkikalli*
*10197 S. Stephen Place, Highlands Ranch, CO 80130*
*TEL: 303-346-2502, MOBILE: 303-478-1028*
*E-MAIL: jmakikalli@comcast.net*

## ፈረንሳይ
የክብር ቆንስል *Jeffrey Richards*
*600 Grant St., Ste. 620, Denver, CO 80203*
*TEL: 303-862-3808*
*E-MAIL: jrichards@ahrs-law.com*

## ጀርመን
የክብር ቆንስል *Paul T. Maricle*
*999 18th St., Ste. 3-1500, Denver, CO 80202*
*TEL: 720-381-1319*
*E-MAIL: pmaricle@cp2law.com*

## *ጓቲማላ




የክብር ቆንስል *Juan Fernando Valey*
*1001 S. Monaco Parkway, Ste. 300*
*Denver, CO 80224*
*www.consdenver.minex.gov.gt*
*TEL: 303-629-9212*
*FAX: 303-629-9211*
*E-MAIL: jvaley@minex.gob.gt*

## ሀንጋሪ

የክብር ቆንስል *Krisztina (Cissie) Megyesy*
*1515 Wynkoop St., Ste. 710, Denver, CO 80202*
*TEL: 303-482-2318*
*E-MAIL: cmegyesy@gmail.com*

## አይስላንድ

የክብር ቆንስል *Ingibjorg Marian (Maja) Stefansdottir*
*202 Spring St, P.O. Box 542, Morrison, CO 80465*
*TEL: 303-465-8586*
*E-MAIL: isconsulco@gmail.com*

## አየርላንድ

የክብር ቆንስል *James M. Lyons*
*1200 17th St., Ste. 3000, Denver, CO 80202*
*TEL: 303-623-9000, DIRECT: 303-628-9546*
*E-MAIL: jlyons@LRRLaw.com; jmartinez@LRRLaw.com*

## ጣሊያን

የክብር ቆንስል *Giovanna Carriero-Contreras*
*360 Acoma St., Denver, CO 80223*
*TEL: 303-274-2634*
*EMAIL: gcontreras@cecsols.com*

## *ጃፓን




ቆንስል ጄነራል *Makoto Ito*
የጃፓን ቆንስላ-ጄነራል,
*1225 17th St., Ste. 3000*
*Denver, CO 80202*
*TEL: 303-534-1151*
*FAX: 303-534-3393*
*E-MAIL: tomie.eilers@de.mofa.go.jp*

## ለግዘምበርግ

የክብር ቆንስል *Jeff Weltzin*
*P.O. Box 270400, Louisville, CO 80027*
*TEL: 720-890-8343, MOBILE: 303-810-5613*
*E-MAIL: jeff.weltzin@flour.com*

## * ሜክሲኮ




ቆንስል ጀነራል *Carlos Bello*
*5350 Leetsdale Dr., Ste. 100*
*Denver, CO 80246*
*portal.sre.gob.mx/denver/*
*TEL: 303-331-1110 x. 101*
*FAX: 303-331-0169*
*E-MAIL: cbello@sre.gob.mx; infodenver@sre.gob.mx*

ምክትል ቆንስል ጀነራል *Jeremias Guzman*
*TEL: 303-331-1110*
*FAX: 303-331-0169*
*E-MAIL: infodenver@sre.gob.mx*

## ሞንጎልያ

የክብር ቆንስል *James Wagenlander*
*1700 Broadway, Ste. 1202, Denver, CO 80290*
*TEL: 303-832-6511*
*E-MAIL: wagenlander@wagenlander.com*

## ሞሮኮ

የክብር ቆንስል *Josh Hanfling*
*500 Williams St., Ste. D, Denver, CO 80218*
*TEL: 303-800-4500, MOBILE: 303-931-5674*
*E-MAIL: joshh@hanfling.com*

## ኔዘርላንድስ

የክብር ቆንስል *Prof. ir. M. (Max) Peeters (ret.);* ረዳት ቆንስል *Mariette van Engelen*
*1127 Auraria Pkwy., Ste. 6, Denver, CO 80204*
*TEL: 720-460-9226*
*E-MAIL: denver@nlconsulate.com*

## ኒካራግዋ

የክብር ቆንስል *Bronwyn Bateman*
*1133 Race St., Ste. 17N, Denver, CO 80206*
*TEL: 303-916-1888*
*E-MAIL: bronwyn.bateman@comcast.net*

## ኖርወይ

የክብር ቆንስል *Rita I. Ehrmann*
*Denver Financial Center, Ste. 1445, 1775 Sherman St., Denver, CO 80203*
*TEL: 303-830-1970*
*E-MAIL: rehrmann@norconden.org*

## * ፔሩ




ቆንስል ጄነራል፣ ሚኒስትር *Eduardo Barandiarán B.*
*6795 E. Tennessee Ave., Ste. 550*
*Denver, CO 80224*
*www.consuladoperu.com*
*TEL: 303-355-8555*
*TOLL FREE: 1-866-788-0338*
*FAX: 303-355-8003*
*E-MAIL: e.barandiaran@consuladoperu.net*

## ፖላንድ

የክብር ቆንስል*Tomasz Skotnicki*
*528 Williams St., Denver, CO 80218*
*TEL: 303-485-6620, MOBILE: 303-517-1278*
*E-MAIL: tskotnicki@aol.com*

## ኮርያ ሪፐብሊክ

የክብር ቆንስል *James W. McGibney*
*1700 Lincoln St., Ste. 4100, Denver, CO 80203*
*TEL: 303-720-1954*
*E-MAIL: jmcgibney@earthlink.net*

## ሩስያ

የክብር ቆንስል *General Deborah A. Palmieri, Ph.D.*
*1552 Pennsylvania St., Denver, CO 80203*
*TEL/FAX: 303-831-9181*
*E-MAIL: deb@DebPalmieriRussia.com*

## ሰርቢያ

የክብር ቆንስል *Steven H. Katich*
*CO Center, 2000 South CO Blvd., Tower One, Ste. 12000, Denver, CO 80222*
*TEL: 303-300-7887, FAX: 303-339-4695*
*E-MAIL: stevenkatich@gmail.com*

## ስሎቫክ ሪፐብሊክ

የክብር ቆንስል *Gregory Fasing*
*44 Cook St., Ste. 100, Denver, CO 80220; P.O. Box 200340, Denver, CO 80220*
*TEL: 303-692-8833*
*E-MAIL: consulden@aol.com*

## ስሎቬንያ

የክብር ቆንስል *Lucky Vidmar*
*1200 17th St., Ste. 1500, Denver, CO 80202*
*TEL: 303-899-7328*
*E-MAIL: vidmar@slovenia-colorado.com*

## ስፐይን

የክብር ቆንስል *Pepe Parrado*
*2158 S. Parfet Dr., Lakewood, CO 80227*
*TEL: 720-934-8933*
*E-MAIL: pepe.parrado@comcast.net*

## ስዊድን

ቆንስል *Donald G. Peterson*
*1720 S. Bellaire St., Ste. 530, Denver, CO 80222*
*TEL: 303-758-0999*
*E-MAIL: denver@consulateofsweden.org*

## ስዊዘርላንድ

የክብር ቆንስል *Dr. Walter Wyss*
*2810 Iliff St., Boulder, CO 80305*
*TEL: 303-499-5641*
*E-MAIL: walter.wyss@colorado.edu*

## ታይላንድ

የክብር ቆንስል *General Donald W. Ringsby*
*1336 Glenarm Place, Ste. 200, Denver, CO 80204*
*TEL: 303-885-5948*
*E-MAIL: consuldwr@aol.com*

## ዩጋንዳ

የክብር ቆንስል *Michael J. Koepke,*
*P. O. Box 1203, Parker, CO 80134*
*TEL: 303-887-5869*
*E-MAIL: mkoepke@usbsinc.com*

## * ዩናይትድ ኪንግደም




ቆንስል-ጄነራል *Erin Kuhn*
*UK Government Office*
*1888 Sherman St., Ste. 200*
*Denver, CO 80203*
*TEL: 720-538-0381*
*FAX: 303-536-5023*
*E-MAIL: ukgo.denver@fco.gov.uk*

# አጭር ማጣቀሻዎች እና ሪፈራሎች

**211 Colorado**

- (በ 211 ይደውሉ) ወይም (866) 760-6489
- የ የዴንቨር የጥሪ ማእከል በ በማይል ኃይ ዩናይትድ Mile High United መንገድ የሚንቀሳቀስ፣ በዚህ ቁጥርም 303-561-2111 ይገኛል። መስማት የተሳኖት ከሆኑ፣ ወደ 2-1-1 ለመድረስ በ ሪሌይ ኮሎራዶ Relay Colorado (7-1-1) ወይም በ 1-800-659-2656 አማካኝነት መደወል ይችላሉ።
- ከክፍያ ነጻ ቀጥታ መስመር ለጤና እና ለሰብአዊ አገልግሎቶች መረጃ ወይም ሪፈራል። የስልክ ጥሪዎች ሚስጢራቸው የተጠበቀ ነው። ከህያ በላይ ለሚሆኑ ቋንቋዎች አስተርጓሚዎች እናቀርባለን፣ አብዛኞቹ የጥሪ ማእከሎች ደግሞ ስፓኒሽ መናር የሚችሉ የሪፈራል ስፔሻሊስቶች አሉዋቸው።
- *https://211colorado.communityos.org/cms/home*

**311 Help Center (Denver)**

- (በ 311 ይደውሉ)
  ከዴንቨር ውጪ: 720-913-1311
- የከተማ ኤጀንሲዎች፣ የመረጃ ምንጮች፣ ፍጻሜዎች፣ እና ሌሎችን ጨምሮ ለሁሉም የከተማ አገልግሎቶች የሚሆኑ የመስመርላይ እና የስልክ ሪፈራሎች።
- *https://www.denvergov.org/content/denvergov/en/denver-311-help-center.html*

**The Center for Trauma and Resilience** (አስተዳደር)

- P.O. Box 18975 Denver, CO 80218
- 303-860-0660 (Administration)
  24-ሰአት የኢንግሊዝኛ ቀጥታ መስመር: 303-894-8000
  24-ሰአት የስፓኒሽ ቀጥታመስመር: 303-718-8289
- 7-1-1 Relay Colorado መስማት ለተሳናቸው
- የወንጀል ሰለባ ድጋፍ፣ ያለመረጋጋት ኢንተርቬንሽን እና የምክር አገልግሎት፣ እንዲሁም ለወንጀል ሰለባዎች የሚደረግ የአደጋ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ። በተጨማሪ የቤት ውስጥ ጥቃት እንዲሁም ጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ሕጋዊ ቀዋሚ የመኖርያ እድል እንዲያገኙ እገዛ የሚያደርግ የህጋዊ ስደት ክሊኒክ (Legal Immigration Clinic) አገልግሎትም ይሰጣል። አስተርጓሚዎች አሉ።
- *www.traumahealth.org*

**Colorado PEAK (Colorado Department of Human Services)**

- የህክምና፣ ምግብ፣ እና የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ጨምሮ ሌሎች Colorado ላይ የሚሰጡ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች የማግኘት ተገቢነት (eligibility) ለመወሰን የሚያስችል የመስመርላይ ቅጽ። በስፓንሽ ቋንቋ የተዘጋጀ ድረገጽም አለ።
- *http://coloradopeak.force.com/*

**Colorado Immigrant Rights Coalition (CIRC)**

- 2525 W. Alameda Ave., Ste. 300, Denver, CO 80219
- 303-922-3344
- ወደ ሌሎች የስደተኞች አገልግሎት አቅራቢዎች የሪፈራል አገልግሎት ጭምር የሚሰጡ የስደተኞች መብት ተማጓች ድርጅቶች። ስፓኒሽ የሚናገሩ ሰራተኞች።
- *http://www.coloradoimmigrant.org/*

**Consular Corps of Colorado**

- የውጭ ቆንስላዎች ዝርዝር ለማየት ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ። የህግ ችግሮች፣ የስራቦታ ጉዳዮች፣ የጤና እንክብካቤ የማግኘት ድጋፍ፣ ወዘተ ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለስደተኞች የሚሰጡ እገዛዎች እና ሪፈራሎች።
- *http://www.consularcorpscolorado.org/members*

**Denver Health Nurse Line**

- 24/7 Hotline: 303-739-1211
- ለፈጣን የህክምና ምክር ይደውሉ። አገልግሎቱም ለዴንቬር የጤና ታማሚዎች እና ለዴንቬር ነዋሪዎች ተሰጥቷል። የህክምና ሠራተኛው ከህክምና ድጋፍ፣ የእንክብካቤ ምክር፣ እና ከሃኪም ጋር ተጨማሪ ህክምና ማስፈለጉን አሊያም አለማስፈለጉ ላይ እርዳታ መስጠት ይችላል።
- *http://www.denverhealth.org/medical-services/emergency-services/nurseline*

**Denver Office of Immigrant and Refugee Affairs**

- Wellington E. Webb Municipal Office Building
  201 West Colfax Avenue, Denver, CO 80202
- Phone: 720-913-8471
- Fax: 720-913-8470
- የዴንቬር የስደተኞች ባለሥልጣን እና የስደተኛ ጉዳዮች ታላቅ ንቃትን እና የስደተኛ እና በዴንቬር የሚኖር ስደተኛን ያስተዋውቃል።
- *https://www.denvergov.org/content/denvergov/en/human-rights-and-community-partnerships/our-offices/immigrant-and-refugee-affairs.html*

**Rocky Mountain Crisis Partners**

- የችግር ጊዜ መስመር: 1-844-493-8255
- ለአእምሮ ጤና፣ አደንዛዥ ነገሮች ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ ችግሮች፣ እቤት ውስጥ፣ ስራ ላይ ወይም ትምህርትቤት ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚሆኑ መረጃዎች እና ሪፈራሎች የሚያገለግል ከክፍያ ነጻ እና ሚስጢሩ የተጠበቀ 24/7 ቀጥታ መስመር። ኢንግሊዝኛ ለማይናገሩ ሰዎች ከ150 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።
- *http://www.metrocrisisservices.org/*

**National Suicide Prevention Lifeline**

- የችግር ጊዜ መስመር: 1-800-273-8255
  ስፓኒሽ: 1-888-628-9454
- ለማንኛውም ውስጡ የተረበሸ እና ስነአእምሮአዊ ጭንቀት ውስጥ የሚገኝ ሰው ከክፍያ ነጻ እና ሚስጢራውነቱ የተጠበቀ 24/7 የራስ ሂወት በራስ ማጥፋትን የመከላከል አገልግሎት የሚሰጥ ቀጥታ መስመር። የአቅራቢዎች ድጋፍ እና ሪፈራሎች። ኢንግሊዝኛ ለማይናገሩ ሰዎች ከ150 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።
- *http://www.suicidepreventionlifeline.org/*

**RAINN- Rape, Abuse & Incest National Network**

- ብሄራዊ የጾታዊ ጥቃት ቀጥታ መስመር (Hotline): 1-800-656-ተስፋ (4673)
- የአስገድዶ መድፈር፣ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት እና በዘመድ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች ከክፍያ ነጻ፣ 24/7 ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ የቀጥታ መስመር። ያለመረጋጋት ድጋፍ፣ ሪፈራሎች እና መረጃ ያቀርባል።
- *http://rainn.org/*

**USCIS- Welcome to the United States**

- ይህ በ UCIS የተዘጋጀ መረጃ ሰጪ ጽሁፍ (guide) ስደተኞች ሂወታቸው ከዩናይትድ ስቴትስ ሁኔታዎች ጋር ለማለማመድ የሚያስችላቸው በተግባር የሚሰራ መረጃ አቅርቦላቸዋል። ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስላለው የቀንተቀን ሂወት እና ስነዜጋ እና መንግስት የሚመለከት መነሻ መረጃ ጭምር አካትቶ ይዟል። ይህ መረጃ ሰጪ ጽሁፍ (guide) በኢንግሊዝኛ፣ አረብኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሃይቲያን ክሬኦሌ፣ ኮርያኛ፣ ፖሊሽ፣ ፖርቱጊዝ፣ ሩስያኛ፣ ሶማሊኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ታጋሎግ፣ ኡርዱ እና ቬትናሚኛ ተዘጋጅቷል።
- *http://www.uscis.gov/tools/settling-us/welcome-united-states*

# የጉዳይ አስተዳዳር/የብዙ አገልግሎት ኤጀንሲዎች

የኬዝ አስተዳደር በአብዛኞቹ ስደተኞች እና ከሀገራቸው ሸሽተው የመጡ ሰዎች ላይ ለሚታዩ ዘረፈ ብዙ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚደረጉ ብዙ አገልግሎቶች እና ሪፈራሎችን ይመለከታል። እነዚህ ድርጅቶች የጤና እንክብካቤ፣ መኖርያ ቤት፣ ስራ፣ ቋንቋ ፣ ትምህርት፣ የህግ ድጋፍ፣ እና ሌሎች በተመለከተ ምክር በመስጠት ግለሰቦችን ይረዳሉ።

**African Community Center (ከሃገራቸው ሸሽተው ለመጡ ብቻ)**

- 5250 Leetsdale Dr., Ste. 200
  Denver, CO 80246
- 303-399-4500
- ከስራ፣ መኖርያ ቤት፣ እንዲሁም የባህል ማስተካኪያ ጋር የተያያዙ የተለያዩ አገልግሎቶች እና የኬዝ አስተዳደር አገልግሎት ከሀገራቸው ሸሽተው ለመጡ ሰዎች የሚያቀርብ መንግስታዊ መልሶ ማስፈር ፕሮግራም (Official Refugee Resettlement program)። አማርኛ፣ አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሂንዲ፣ ስዋሂሊ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሊ፣ ካረን እና ትግርኛን ጨምሮ በ 26 ቋንቋዎች የሚሰሩ ሰራተኞች አሉ።
- *http://www.acc-den.org*

**Centro San Juan Diego**

- 2830 Lawrence St.
  Denver, CO 80205
- 303-295-9470
- ቢዬንስታር Bienestar የቤተሰብ አገልግሎቶች: 303-297-8696
- ሰፊ የጤና እና የአዋቂዎች ትምህርት አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ከመኖርያ ቤት፣ ግብር፣ የህግ ምክር፣ ዜግነት፣ የጀማሪ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ESL፣ GED፣ እና የኮምፒዩተር ክህሎቶች ጋር የተያያዙ እገዛዎች። ለአዳዲስ ስደተኞች እገዛ እና ድጋፍ ያቀርባል። ስፓኒሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞችም አሉ።
- *http://www.centrosanjuandiego.org/*

**Church in the City**

- ቤተክርስቲያን የሚገኝበት ቦታ: 1580 Gaylord St., Denver, CO 80206
- ጽህፈትቤቶች: 2280 E. 16th Ave., Denver, CO 80206
- 303-322-5733
- ለርሀብ ለተጋለጡ እና ቤትአልባ ለሆኑ ግለሰቦች የምግብ ባንክ እና ከክፍያ ነጻ ምግቦችን ያቀርባል፣ የጤና እንክብካቤ አያያዝ፣ እና ESL፣ ስፓኒሽ፣ እንዲሁም የኮምፒዩተር ትምህርቶች ይሰጣል። ለአባሎች ተጨማሪ አገልግሎቶች እና እገዛዎች ይሰጣል። ስፓኒሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞችም አሉ።
- *http://churchinthecity.org/*

**Colorado African Organization**

- 6795 E. Tennessee Ave., Ste. 250
  Denver, CO 80224
- 303-953-7060
- አፍሪካዊ ለሆኑ ከሀገራቸው ሸሽተው የመጡ ሰዎች፣ ጥገኝነት የተፈቀደላቸው ሰዎች፣ ስደተኞች እና ቤተሰቦቻቸው የኬዝ አስተዳደር አገልግሎት ይሰጣል። የጤና ትምህርት እና የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል እና ትምህርት አገልግሎትም ይሰጣል። በተጨማሪ የኢንግሊዝኛ ትምህርት እና የአዋቂዎች ትምህርት፣ እንዲሁም የአድቮኬሲ እና ውህደት እገዛ ይሰጣል።
- *http://www.caoden.org/*

**Colorado People's Alliance**

- 1085 Peoria St. Aurora, CO 80011
- 700 Kalamath St, Denver, CO 80204
- 303-893-3500
- ስደተኞች መብታቸው እንዲረዱ የሚያግዙ ዎርክሾፖች (የህጋዊ ወረቀት የሌላቸው) በመላ ክፍለሀገሩ ይደረጋሉ። የዜግነት እና ESL ትምህርቶች ያቀርባል። ስፓኒሽ የሚናገሩ ሰራተኞች አሉ።
- *https://coloradopeoplesalliance.org/*

**Denver Urban Matters**

- 1717 E. Colfax Ave.
  Denver, CO 80218
- 303-355-4896
- ከመኖርያ ቤት፣ መገልገያዎች፣ እና ስራ ጋር የተያያዘ እገዛ እንዲሁም ወደሌላ ኤጀንሲዎች ሪፈራል የመስጠት ስራዎች። እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የአደጋ ጊዜ እና የማረጋጋት አገልግሎቶች ይሰጣል፣ እንዲሁም ነጻ የህግ መብቶች። ስፓኒሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞችም አሉ።
- *http://www.denum.org/*

**El Centro Humanitario**

- 2260 California St.
  Denver, CO 80205
- 303-292-4115
- የስራ እገዛ እና የሰራተኛ ሀይል ልማት/ትምህርት ፕሮግራሞች፣ የደሞዝ ስርቆት ክሊኒኮች። ሰራተኞቹ ስፓኒሽም ይናገራሉ።
- የሥራ ድጋር፣ የሥራ ችሎታን ማሳደጊያ፣ እና የትምህርት መርኃግብሮችን፣ ደሞዝ የሚሰርቁ ኪሊኒክ፣ እና በአከባቢው ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የሴቶች መርኃግብር። ሠራተኛው የስፓንስ ቋንቋን ይናገራል።
- *http://www.centrohumanitario.org/*

**Jewish Family Service**

- 3201 S. Tamarac Dr.
  Denver, CO 80231
- 303-597-5000
- የአደጋ ጊዜ እርዳታ ቀጥታ መስመር (Hotline): 720-248-4716
- እንደ የአእምሮ ጤና የምክር አገልግሎት፣ የዜግነት ትምህርቶች፣ እና የምግብ ማከማቻዎች የመሳሰሉ አገልግሎቶች ለስደተኞች እና ከሀገራቸው ሸሽተው ለመጡ ሰዎች ይሰጣል። ፋርሲ፣ ጀርመንኛ፣ ሩስያኛ፣ ስፓኒሽ፣ ዩክሬንኛ፣ እንዲሁም ያዲሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞች አሉ። ለሌሎች ቋንቋዎች ደግሞ አስተርጓሚዎች እንጠቀማለን።
- *http://jewishfamilyservice.org/*

**Lutheran Family Services**

- 1600 Downing St., Ste. 600
  Denver, CO 80218
- 303-980-5400
- ከቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታ፣ ስራ ማጽደቅ፣ ዜግነት በህግ ማግኘት፣ እንዲሁም ቪዛ ጋር የተያያዙ የህግ አገልግሎቶች ለስደተኞች። በተጨማሪ ከሀገራቸው ሸሽተው ለመጡ ሰዎች የመልሶ ማስፈር እና ኬዝ አስተዳደር አገልግሎቶች እንሰጣለን። የምንጠቀምባቸው ቋንቋዎች ኤፍ-ሜይ፣ አማሪኛ፣ ቦሲንያኛ/ክሮሺያኛ/ሰርቢያኛ፣ በርሚስ፣ ኢንግልዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ግሬቦ፣ ኪኮንጎ፣ ኪቱባ፣ ክሪዮ፣ ሜንዴ፣ ፒዩላር (ፉላኒ)፣ ሩስያኛ፣ ስሎቬኒ፣ ሶማሊኛ (Af-Maxaa)፣ ስፓኒሽ፣ ስዋሂሊ፣ ቴምኔ፣ ታይ፣ ሺሉባ፣ ዩክሬንኛ፣ እና ዎሎፍ ያጠቃልላሉ።
- *http://www.lfsco.org/*

**Mi Casa Resource Center**

- 360 Acoma St.
  Denver, CO 80223
- 303-573-1302
- አገልግሎቶቹ ነጻ ጂኢዲ GED እና የጀማሪ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ESL ትምህርቶች፣ የስራ እገዛ፣ የህግ መብቶች (የስደተኞች ጉዳይ፣ የፋይናስ ጉዳዮች፣ መኖሪያ ቤት፣ ስራ፣ እና የቤተሰብ ህግ የሚሸፍኑ)፣ የኢንተርፕሩነር ትምህርቶች፣ የስራ ብድሮች፣ እንዲሁም በምግብ እና መዝናኛ ስራ፣ ኮንስትራክሽን፣ እንዲሁም የ CDL ፈቃዶች የስራ ማጠናከርያ ስልጠና የሚያጠቃልሉ ናቸው። የተወሰኑ አገልግሎቶች በስፓኒሽም ይሰጣሉ።
- በአራት ቦታዎች ላይ የሚሰጡት አገልግሎቶች ነጻ GED እና ESL ክፍሎችን፣ የሥራ ድጋፍ፣ ሕጋዊ ምሽቶች፣ የሥራ ፈጠራ ትምህርቶች፣ የሥራ ብድር፣ እና በእንግዳ ተቀባይነት የሥራ ዕድገት ሥልጠና፣ ግንባታ፣ እና የCDL ፈቃዶችን ያጠቃልላል። አንዳንድ አገልግሎቶች በስፓንሽ ቋንቋ ይሰጣል።
- *http://www.micasaresourcecenter.org/*

**One Colorado**

- 1490 Lafayette St., Ste. 304
  Denver, CO 80218
- 303-396-6170
- የኢሚግሬሽን እና የመባረር ስጋት ላበቻው LGBT ግለሰቦች እና ቤተሰቦች መረጃ እና ሪፈራሎችን ለመስጠት ከ Colorado Immigrant Rights Coalition (CIRC) ጋር ተባብሮ ይሰራል። ባጠቃላይ LGBT ማበረሰብ ላይ የሚደረግ ከስራ እና ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዘ የማዳላት ተግባር በተመለከተ እገዛ ይሰጣል፣ እንዲሁም የጤና እንክብካ እንዲያገኙ እና ሌላም አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል።
- መረጃን እና ለ LGBT ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የሚላክበት ከስደተኛ እና መልሶ ስለመላክ ሀሳቦች ጋር ይሰጣል። በስፋት ለ LGBT ማኅበረሰብ እርዳታን፣ ሥራ ማግኘት ላይ እና ቤት በማግኘት ላይ በመገለል ጉዳዮችን አካቶ እርዳታን ይሰጣል፤ የጤና እንክብካቤ፣ እና ሌላም ተጨማሪ አገልግሎት ለማግኘት እርዳታ ይሰጣል።
- *http://www.one-colorado.org/*

**Servicios de la Raza**

- 3131 W. 14th Ave
  Denver, CO 80204
- 303-458-5851
- ለአዋቂዎች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች፣ እቤት ውስጥ ወንጀል ለተፈጸመባቸው ሰለባዎች እገዛ፣ ኤችአይቪ/ኤድስ ላለባቸው ሰዎች የኬዝ አስተዳደር አገልግሎት፣ እንዲሁም የወጣቶች ፕሮግራሞች። በተጨማሪ የህዝብ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ከማግኘት እና ቅጾችን ከመሙላት የተያያዘ ድጋፍ ያደርጋል። ስፓኒሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞችም አሉ።
- *http://serviciosdelaraza.org/*

**Spring Institute for Intercultural Learning**

- 1373 Grant St.
  Denver, CO 80203
- 303-863-0188
- የአዋቂ ትምህርት እና የሙያ ትምህርት, ESL, and cultural የቅድመ-ስራ ስልጠና፣ ESL፣ እና የባህል ብዙህነት ግንዛቤ የሚያካትቱ የትምህርት ፕሮግራሞች። ከሀገራቸው ሸሽተው ለመጡ ሰዎች እና ጥገኝነት ለተፈቀዷላቸው ሰዎች ከ Emily Griffith Opportunity School በመተባበር የስራቦታ ዝግጁነት ትምህርቶችን ይሰጣል። በተጨማሪ በ Interpreter Network of Colorado (INoC) አማካኝነት በ 80 ቋንቋዎች የኢንተርፕሪተሽን እና የትርጉም አገልግሎት ያቀርባል። ሰራተኞቻችን የሚናገሩዋቸው ቋንቋዎች አማርኛ፣ አረብኛ፣ ኢንግኒዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሩስያኛ፣ ሶማሊኛ፣ እና ስፓኒሽ ያጠቃልላሉ።
- *http://www.springinstitute.org/*

## የአዋቂዎች ትምህርት

የአዋቂዎች ትምህርት ባጠቃላይ የአዋቂ ተማሪዎች ክህሎት እና እውቀት ለማሻሻል የሚሰጥ ብዙ እንቅስቃሴዎች፣ ግንኙነቶች፣ እና ተቋሞች አጠቃልሎ የያዘ ትምህርት ነው። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የገቡ ስደተኞች ብዙ የትምህርት እና መሀይምነት የማጥፋት ግቦች ይኖራቸዋል። ለእያንዳንዱ ስደተኛ ይህ ልዩ እና ማንኛውም ከኢንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት እስከ የዜግነት ትምህርት የሆነ ነገር ሊያጠቃልል ይችላል። የሚከተሉት ድርጅቶች ከአዋቂ ስደተኞች ጋር በቅርበት በመስራት ነጻ ወይም ዝቅተኛ ክፍያ የሚጠይቅ እገዛም ያቀርባሉ።

**Arapahoe Library District**

- 303-ቤተመጽሀፍት፣ 303-542-7279
- የኢንግሊዝኛ ንግግር ቡድኖች፣ የጀማሪ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ESL ትምህርቶች፣ እና ኮምፒዩተር ትምህርቶች በኢንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ እና በሩስያኛ ቋንቋዎች አራፕሆ ካውንቲ Arapahoe County በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ይሰጣሉ።
- *http://arapahoelibraries.org/*

**Community College of Denver**

- Cherry Creek Building
  1111 West Colfax Ave.
  Denver, CO 80204
- 303-556-2600
- በመካለኛ ደረጃ ለጀመሩ በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የጀማሪ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ESL ትምህርቶች ይሰጣሉ። በተጨማሪ Denver በሚገኙ ሌሎች ቦታዎች ላይ ጂኢዲ GED እና ቅድመ- ጂኢዲ GED ትምህርቶች ይሰጣል።
- *http://www.ccd.edu/*

**Emily Griffith Technical College**

- 1860 Lincoln St.
  Denver, CO 80203
- 720-423-4700
- የ ESL ስህፈትቤት ቁጥር: 720-423-4750
- ESL፣ GED፣ እና የስራ-ክህሎቶች ትምህርቶች፣ እንዲሁም የሙያ እና ሰርትፊኬሽን ፕሮግራሞች። ስልክ በመደወል ስለ ክፍያዎች እና የግዜ ሰሌዳዎች መረጃ ያግኙ፣ እንዲሁም የክፍያ ግምገማ ፈተናዎች እንዲዘጋጅልዎ ያድርጉ።   ነጻ የትምህርት ዕድል ይሰጣል
- *http://www.emilygriffith.edu/language*

**Focus Points Family Resource Center**

- 2501 E. 48th Ave.
  Denver, CO 80216
- 303-292-0770
- ከላቲኖ ህዝቦች መስራት ከሚችሉ ባለሙያዎች የታጀቡ ሰፋፊ ፕሮግራሞች እና ትምህርቶች ለአዋቂዎች፣ ህጻናት፣ እና ቤተሰቦች። የሚሰጡት የትምህርት አይነቶች ESL፣ GED (በኢንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ)፣ መሰረታዊ ትምህርት ለአዋቂዎች፣ ገና በህጻንነት ገዜ የሚሰጥ ተትምህርት፣ ስራ፣ ልጅ አስተዳደግ፣ እና ሌሎችን ያጠቃልላሉ።
- *http://www.focuspoints.org/*

Rev 11/16

**Intercambio de Comunidades**

- 4735 Walnut St. Ste. #B
  Boulder, CO 80301
- 303-996-0275
- የ ESL ትምህርቶች የለያዩ ቦታዎች ላይ ይሰጣሉ፣ ሌሎች የትምህርት አይነቶች (ዜግነት፣ መሰረታዊ የኮምፒዩተር ትምህርት፣ የባህል ልውውጥ) ደግሞ በልደር Boulder/ላፋዬት Lafayette አካባቢ ላይ ይሰጣሉ።
- *http://www.intercambioweb.org/*

**Jefferson County Libraries**

- 10200 W. 20th Ave.
- Lakewood, CO 80215
- 303-922-4683
- የተረት ተረት ክፍለጊዜዎች፣ የስራ ቃለመጠይቅ ዘዴዎች፣ እና የኮምፒዩተር ክህሎቶች የሚያጠቃልሉ የህጻናት ፕሮግራሞች።
- *http://jefferson.lib.co.us/*

**The Learning Source**

- 8790 W. Colfax Ave., Ste. 109
  Lakewood, CO 80215
- 303-922-4683
- የ ESL ትምህርቶች በመላ Denver አከባቢ።
- *http://thelearningsource.org/*

**Community College of Aurora, Lowry Campus**

- 710 Alton Way
- Denver, CO 80230
- 303-340-7093
- ለ CCA  አመልካቾች አዋቀርን፣ ሰዋስዎን፣ እና ንባብን አካቶ ለ ESL መርኃግብር የኮሌጅ ዝግጅት ይሰጣል። ፕሮግራሙን የፈጸሙ ተማሪዎች መፈጸሙን የሚያሳይ ሴርተፊኬት ይቀበላል።

# የቤተሰብ እና ህጻናት አገልግሎቶች

የአሜሪካ የትምህርት ስርአት ዳይናሚክሶች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለሚገቡ ስደተኞች ፈታኝ ሊሆንባቸው ይችላል። ህጻናት ለወላጆቻቸው እንደ አግባቢ ወይም እንደ አስተርጓሚ ሆነው በሚያገለግሉበት ጊዜ ከአዲስ ቋንቋ እና ባህል ጋር እየተላመዱ ሊሄዱ ይችላሉ። ለአዳዲስ ስደተኞች እና ከሀገራቸው ሸሽተው የመጡ ሰዎች የትምህርት መረጃ ምንጮች ማግኘት እና መላመድ ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል። እንደ የትምህርት ምዝገባ፣ የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፣ እንዲሁም ህጻን አስቀድሞ መውሰድ ብዙ አካሄዶች፣ ቅጾች መሙላት፣ ወይም ጉብኝቶች ሊተይቁ ይችላሉ። የሚከተሉት ድርጅቶች ብቁ ለሆኑ ወላጆች አጠቃላይ ምክር፣ የወላጅ ትምህርት፣ የኢንግልዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች፣ ወይም የህጻን እንክብካቤ አገልግሎት ይሰጣሉ።

**Denver Public Schools English Language Acquisition and Newcomer Centers**

- ELA Hotline: 720-423-2040
- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክሎትን ለማግኘት በ DPS ተማሪዎችን የሚረዳ መርኃግብን፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በንቃት መከታተል አለባቸው። አዲስ መጪ ማዕከላት በአምስት ትምህርት ቤቶች የተቀመጡት ለቤተሰቦች እርዳታን እና ድጋፍን ይሰጣሉ። የሚላክበት ቦታ እና ማመልከቻ ያስፈልጋል፤ ለበለጠ መረጃ ይደውሉ።
- *http://ela.dpsk12.org/our-services*

**Denver Preschool Program**

- P.O. Box 40037
  Denver, CO 80204
- 303-595-4377
- info@dpp.org
- ተገቢነት ላላቸው ቤተሰቦች የትምህርት ክፍያን ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን፣ የትምህርት ቤት ደረጃ ማውጣቶችን፣ ግለታሪኮችን፣ እና የመግቢያ መረጃን ይሰጣል። ድኅረገጾች በእንግሊዝኛ እና በስፓንሽ ቋንቋ ይገኛል።
- *http://www.dpp.org*

**Focus Points Family Resource Center**

- 2501 E. 48th Ave.
  Denver, CO 80216
- 303-292-0770
- ተጨማሪ መርኃግብሮችን እና ለአዋቂ ሰዎች፣ ለልጆች፣ እና ለቤተሰብ፣ የላቲን ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ጋር በሥራ ላይ የሚገኙትን ባለሙያዎች ጋር ትምህርት ይሰጣል። ትምህርቱም ESL, GED (በእንግሊዝኛ እና በስፓንሽ  ቋንቋ)፣ የአዋቂዎች መሰረታዊ ትምህርት፣ የልጆች ትምህርት፣ ሥራ፣ ወላጅነት፣ እና ሌሎችንም ያጠቃልላል።
- *http://www.focuspoints.org/*

**Gathering Place**

- 1535 High St.
  Denver, CO 80218
- 303-321-4198
- በድኅነት እና በቤት እጦት እየተሰቃዩ ላሉት ለሴቶች፣ለልጆች፣ እና ጾታቸውን ለለወጡ ግለሰቦች ማስቀመጫ ማዕከላትን ይሰጣል።  በርካታ በደህና ሁኔታ ላይ የመሆን አገልግሎቶች የሚያጠቃልለው የ GED ዝግጅት፣ የሥራ ዝግጁነት፣ የኮምፒውተር ላብራቶር፣ የምግብ እና የንጽሕና መጠበቂያ ዕቃዎች፣ ልብስ እና ሌሎች ነገሮችን ነው።  ስፓንሽ ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኞች ይገኛሉ።
- *http://www.tgpdenver.org/*

**Metro Denver Bright Beginnings**

- 3605 Martin Luther King Jr. Blvd., Denver, CO 80207
- 303-433-6200
- ከቅድመወሊድ እስከ 3 አመት የህጻን እድሜ ያለው የህጻን እድገት የሚሸፍኑ የትምህርት እና የድጋፍ መገልገያዎች ለወላጆች። ስፓኒሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞች አሉ። ለቤት ጉብኝት ጥያቄ ለማቅረብ ይደውሉ ወይም ድሳረገጻችንን ይጎብኙ።
- *http://brightbythree.org* ወይም "BRIGHT" የሚለውን ቃል ወደ 444999 ቁጥር ላይ መላክ ይችላሉ።

**Scholars Unlimited**

- 3401 Quebec St., Ste. 5010
  Denver, CO 80207
- 303-355-0290
- አነስተኛ ገቢ ያላቸው ልጆች እና የትምህርት ችግር ያለባቸውን ከትምህርት ቤት በኋላ እና በክረምት የትምህርት እገዛ ፕሮግራሞች ይሰጣል። የመጻፍ እና የማንበብ -ትኩረት የተደረገበት ያካታል እና STEM - ስጦታዎችን ያበቃል። የመመዝገብ መረጃን ለማግኘት በኢሜል info@ scholarsunlimited.org ላይ ይላኩ።
- *http://www.scholarsunlimited.org*

ስደተኞች የማይናቁ የስራ ኃይሉ አካል ናቸው። ውጭ የተወለዱ ግለሰቦች 16.3% የዩ.ኤስ. የስራ ኃይል የሚሸፍኑ ሲሆን 25% ገደማ የሚሆኑት ውጭ የተወለዱ ሰራተኞች በአገልግሎቱ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው ይገኛሉ። በተጨማሪ፣ እዚሁ ውስጥ 17% አዳዲስ የንግድ ስራ ባለቤቶች ስደተኞች ናቸው። በርግጥም፣ ከዩ.ኤስ. የሰራተኞች ስታትስቲክት ቢሮ (2013) በተገኘ መረጃ መሰረት፣ ስደተኞች በ ዴንቨር Denver የከተማ አከባቢ የአነስተኛ የንግድ ስራ ባለቤት የመሆን እድላቸው ዩ.ኤስ. ውስጥ ከተወለዱ ዜጎች በ 10% የላቀ ነው። ከታች የተዘረዘሩት ድርጅቶች ከስራ ፍለጋ፣ ከስራቦታ ጋር የተያያዙ የህግ እና የደህንነት ጉዳዮች፣ አጠቃላይ የስራ ዝግጁነት፣ እና ሌላ እገዛ ያደርጋሉ።

**9to5 National Association of Working Women**

- 1634 Downing St., Unit A
  Denver, CO 80218
- 303-628-0925
- የ National Job Survival ቀጥታ መስመር (Hotline): 1-800-522-0925
- ሴት ሰራቶኞች ላይ ጥኩረት የሚያደርግ የሰራተኞች መብቶች የተመለከቱ መረጃዎች የሚሰጥ እና የስራላይ ግጭቶች ለመፍታት የሚሰራ የስራ እገዛ ሰጪ ቀጥታ መስመር (hotline)። ጾታዊ ትንኮሳ እና አድልዎ ላይ ስልጠና ይሰጣል። አስቀድሞ ካሳወቁ በስፓኒሽ ቋንቋም ስልጠና ይዘጋጅልዎታል።
- *http://9to5.org/local-chapters/9to5-colorado/*

**Center for Work Education and Employment (CWEE)**

- 1175 Osage St., Ste. 300
  Denver, CO 80204
- 303-892-8444
- እንደ የኮምፒዩተር ትምህርት፣ የ GED ዝግጁነት፣ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች ራስን በራስ መገምገም የመሳሰሉ የስራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች። ይህ የካውንቲ ኬዝ አስተዳዳሪዎችን ሪፈራል ይጠይቃል። ሙሉ የኢንግሊዝኛ ችሎታም ሊጠይቅ ይችላል።
- *http://www.cwee.org*

**El Centro Humanitario Para los Trabajadores**

- 2260 California St.
  Denver, CO 80205
- 303-292-4115
- Colorado ላይ የሚሰሩ የቀን ሰራተኞች መብቶቻቸው እና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን በትምህርት፣ የስራ ክህሎት፣ የአመራር እድገት፣ የህብረት እርምጃ እና አድቮኬሲ አማካኝት ይሰራል።
- *http://www.centrohumanitario.org*

**Occupational Safety and Health Administration (OSHA)**

- Cesar Chavez Memorial Building
  1244 Speer Blvd., Ste. 551
  Denver, Colorado 80204
- 303-844-5285
- ከሥራ ሰዓት ውጪ ለመደወል: 1-800-321-OSHA (6742)
- የደህንነት ስጋቶች፣ አድልዎ፣ በደል፣ ወይም ሌሎች ስራቦታ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት ስጋቶችን በተመለከተ እገዛ መስጠት። ችግሮች እና አደጋዎችን በተቻለ መጠን ፈጥኖ ሪፖርት ማድረግ፣ ፈጣን ምርመራ እንዲደረግ እና የሰራተኞች ደህንነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ረገድ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ሰራተኞች አደጋዎችን በዝርዝር መዝግበው መያዝ መቻል አለባቸው።
- *https://www.osha.gov/*

**Unite Here**

- Colorado Affiliates: Local 23, c/o Kevin Abels
  5303 E. Evans Ave., Ste. 302
  Denver, CO 80222
- 303-759-5458
- እንደ ሄቴሎች፣ ምግብ ቤቶች፣ አውሮፕላን ማረፊያዎች፣ እና የኢንዱስትሪ ልብስ እጥበት ቤቶች በመሳሰሉ የአገልግሎት ዘርፍ ስራዎች ለተሰማሩ ሰራተኞች በማህበራት መወከል። በተጨማሪ የሰራተኞች መብቶች፣ የማህበር ምስረታ፣ እና ፖለቲካዊ እርምጃ መውሰድ በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። ስፓንሽ መናገር የሚችሉ ሰራተኞች አሉ።
- *http://www.unitehere.org/*

**Work Options for Women (WOW)**

- 1200 Federal Blvd.
  Denver, CO 80204
- 720-944-1920
  የውስጥ መስመር: 720-944-3393
- የስራ ስልጠና፣ የሂይወት ክህሎቶች፣ እና የኬዝ አስተዳደር ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሴቶች እና TANF እየተቀበሉ ለሚገኙት። ተሳታፊዎች የግድ እድሜአቸው ከ 18 በላይ የሆኑ፣ ዩ.ኤስ. ላይ እንዲሰሩ በህግ የተፈቀደላቸው፣ በሳምንት ለ 40 ሰአታት የሚሰሩ፣ እንዲሁም ብያንስ ለ 90 ቀናቶች ከአደንዛዥ እጾች ነጻ ሆነው የቆዩ መሆን አለባቸው።
- *http://www.workoptions.org/*

**Workforce Centers (Office of Economic Development, City and County of Denver)**

- የሥራ ፍለጋ አገልግልቶችን እና የኮምፒውተ ትምህርቶች። አንዳንድ ፕሮግራሞች የዜግነት ወይም ምን ዓይነት ጥገኝነትን ማሳወቂያ ወረቀቶችን ይፈልጉ።
- *http://www.denvergov.org/WorkforceDevelopment/tabid/435763/Default.aspx*

**Denver Workforce Center at Montbello (Denver County)**

- 4685 Peoria St., Ste. 251
  Denver, CO 80239
- 720-930-4063

**Denver Workforce Center at DIA**

- 8500 Pena Blvd.
  5th Level, Main Terminal, West Side
  Denver, CO 80249
- 303-342-2590

**Denver Workforce Center at Westside**

- 1200 Federal Blvd.
  Denver, CO 80204
- 720-930-4331

**Denver Workforce Center at Eastside**

- 3815 Steele St. (በዴንቬር የሰው አገልግሎቶች መምሪያ ሕንጻ ውስጥ)
  Denver, CO 80205
- 720-924-8205

# ጤና

በአሁኑ ወቅት፣ አንድ ሶስተኛ ስደተኞች የጤና መድህን የላቸውም። ዋናዋናዎቹ የጤና መድህን ከማግኘት የሚያግዱ ምክንያቶች ውስጥ የስደተኛነት ሁኔታ፣ እምነት ማሳደር፣ እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መነሻ ይጠቀሳሉ። የስደተኞች የመጀመሪያ ደረጃ እና መከላከል መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች የመጠቀም ሁኔታ ከሌሎች ጋር ስናነጻጽረው ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለን፣ ወደ አደጋ ጊዜ አገልግሎት መስጫ ክፍል የመሄድ ሁኔታቸው ጭምር ከሌሎች ያነሰ ነው። ምንም እንኳ ስደተኞች ሜዲኬይድ Medicaid ለማግኘት ለመመዝገብ አምስት አመት የመጠበቅ ግዴታ ያለባቸው መሆን እና ሌሎች እንቅፋቶች ቢኖሩም፣ በአሁኑ ጊዜ የተመዘገቡ ስደተኞች አፎርደብል ኬር Affordable Care Act በሚደነግገው መሰረት የህክምና እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው። ይሁን እና አገልግሎቶች አማጥጦ ያለመጠቀም ሁኔታ ይታያል፣ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡ ስራ መሰረት ያደረገ መድህን አለመኖር፣ የባለመብትነት ሁኔታ ላይ ብዥታ መኖር፣ ባህል እና ቋንቋ መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች እጥረት። መድህን ከሌላቸው ስደተኞች ውስጥ ሶስት ሲሶዎቹ የዩ.ኤስ. ዜጎች ሲሆኑ፣ ብዙዎቹ እንደ የማህበረሰብ ጤና ማእከሎች የመሳሰሉ የሴፍቲ ኔት አቅራቢዎች ላይ ጥገኞች ናቸው። እዚህ የተዘረዘሩት ድርጅቶች አካላዊ እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች፣ የጤና ትምህርት፣ የድጋፍ ቡድኖች፣ እና የሪፈራል አገልግሎቶች ያቀርባሉ።

**Asian Pacific Development Center**

- 1537 Alton St.  
